

# ባርኔት የርቀት ትምህርት ቤት

## የድህረ-16 ትምህርት በዩናይትድ ኪንግደም

BELS Barnet Education & Learning Service

BARNET LONDON BOROUGH

# ባርኔት የርቀት ትምህርት ቤት

## መግቢያ

እንኳን ወደ ዩናይትድ ኪንግደም በደህና መጣችሁ!

የዚህ ቡክሌት ዓላማ፡ እንዴት የትምህርት አገልግሎት ማግኘት እንደምትችሉ መረጃ መስጠት እና የተለያዩ የሙያ እና ዕውቀት ዘርፎችን በተመለከት ሓሳቦችን ማካፈል ነው።

አንዳንድ ጊዜ እዚህ ያለው የትምህርት ስርዓት የተወሳሰበ ሊመስል ይችላል፣ እናም ይህ መመሪያ ሁሉም ነገር እንዴት እንደሚሰራ በቀላሉ ለመረዳት ያስችላችኋል የሚል እምነት አለን።



## ይዘቶች

መመሪያው በሚከተሉት 7 ክፍሎች ተከፋፍሎ ቀርቧል፡


1. የትምህርት ስርዓት አጠቃላይ እይታ
2. የድህረ-16 በኋላ የትምህርት መንገዶች ምሳሌ
3. በትምህርታችሁ ላይ የተሳተፉ ቁልፍ ኣዋቂ ሰዎች
4. በኮሌጁ የሚገኙ እድሎች
5. የ21/22 ትምህርት ዓመት የጊዜ ሰሌዳ
6. የምሳሌ ኮሌጅ የጊዜ ሰሌዳ
7. ጠቃሚ ሊንኮች እና አድራሻዎች

## 1. 1. የትምህርት ስርአት አጠቃላይ እይታ

### እንኳን ደህና መጡ!

እዚህ አገር እንደገባችሁ፣ በመኖርያችሁ አቅራቢያ በሚገኝ ኮሌጅ እንድትመዘገቡ ድጋፍ ይደረግላችኋል። በአጠቃላይ የኮሌጅ ትምህርቶች መስከረም ጀምረው ሃምሌ ላይ ይጨርሳሉ። የምትማሩት የመጀመርያው የትምህርት ኣይነት ለሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚሰጥ እንግሊዘኛ ነው ወይም በአጭሩ ኢሶል(ESOL) ይባላል። እነዚህ የኢሶል ትምህርቶች ተጣጣፊ ናቸው፣ ስለዚ አንዳንድ ግዜ ከመስከረም ወር በኋላ ለምሳሊ ጥር ወር ላይ ልትጀምሩ ትችላላችሁ።



የምትማሩት የመጀመርያው የትምህርት የትምህርት ዓይነት ለሌላ ለሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች ተናጋሪዎች የሚሰጥ እንግሊዘኛ ነው ወይም በኣጭሩ ኢሶል (ESOL) ይባላል።

በኮሌጁ ስትመዘገቡ በቅድሚያ የእንግሊዘኛ እና የሂሳብ ችሎታችሁ ይመዘናል። በእንግሊዘኛ እና ሂሳብ ውጤታችሁ በመመርኩስ ከ 1 እስከ 4 ባሉ የ ኢሶል(ESOL) ደረጃዎች በአንዱ ትመደባላችሁ። በኢሶል ትምህርት እንግሊዘኛ (መስማት እና መናገር፡ ማንበብ እና መጻፍ) ሂሳብ እና የኮምፒዩተር (የኮምፒዩተር ቴክኖሎጂ መረጃ) ትምህርት ይሰጣችኋል። አንዳንድ ጊዜም የስራ ተመኩሮዎች ወይም ሌሎች እንቅስቃሴዎች ይኖሯችኋል።

የኢሶል ዋነኛ ክፍል፣ ተማሪዎች በአንድ የትምህርት ዓመት ውስጥ (መስከረም- ሃምሌ) ከ ኢንትሪ 1 ወደ ኢንትሪ 2 ሊዘዋወሩ የሚያስችል ተታጣፊነት ያለው መሆኑ ነው። በመደበኛ የትምህርት አገልግሎቶች ይህ አማራጭ የለም። የኢሶል ተማሪ በአንድ ዓመት ውስጥ ከአንድ ደረጃ ወደ አንዱ የመሸጋገር ሁኔታ፣ በተማሪው ተሳትፎ እና ባሟላቸው የስራ ደረጃዎች ላይ ይመረኮሳል።

ከኢሶል ኢንትሪ ሌቭል 3 በኋላ ምናልባት የሙያ ትምህርት ወይም መደበና ትምህርት ትጀምሩ ይሆና።፡ ለምሳሌ የኤለኪትሪክ መዘርጋት ፡ የቧንቧ መግጠም፡ የመገናኛ ብዙሃን ትምህርት፡ ኮንስትራሽን እና ሌሎች በጣም በጣም ብዙ።

የሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች ከኮሌጅ ወደ ኮሌጅ ይለያያሉ፣ እና እናንተ የመረጣችሁትን መማር ትችላላችሁ!

በተጨማሪም ለሙያ ትምህርት በበለጠ እንድትዘጋጁ የሚያስችላችሁን፣ የኢሶል የበለጠውን የትምህርት ደረጃ፣ ማለት ኢሶል ሌቭል 1ን መማር ትችላላችሁ።

በኢሶል ኢንትሪ 3 የኮሊጃችሁ አስጠኚ/መምህር ስለሚቀጥሉት ደረጃዎች ምክር ይሰጧችኋል። እንዲሁም የፈለጋችሁትን የትምህርት ዓይነት እንድትመርጡ ያግዟችኋል።

## ከኢሶል በኋላ

ከኢሶል በኋላ የሙያ/ መደበኛ ትምህርቶች የተማራቹ፣ ከነን ላይ የሂሳብ እና እንግሊዘኛ ትምህርቶችን መማር ትቀጥላላችሁ።

ይህ በሚከተሉት መንገዶች ሊያድግ ይችላል፡

**ፋንክሽናል ስኪልስ ሌቭል 1 እንግሊዝኛ እና ሂሳብ**

**ፋንክሽናል ስኪልስ ሌቭል 2 እንግሊዝኛ እና ሂሳብ**

**ጂሲኤስኢ(GCSE) እንግሊዘኛ እና ሂሳብ**

የጂሲኤስኢ እንግሊዘኛ እና ሂሳብ ትምህርት ውስጥ ለመግባት የ5-6 ዓመታት ስራ ይጠይቃል።

የደረጃ 1 እና 2 ፋንክሽናል ስኪልስ ሌቭል የብቃት ማረጋገጫ በእንግሊዝኛ እና ሂሳብ ትምህርት ካገናችሁ፣ በኋላ የአፓረንትሺፕ ትምህርት መማርም ትችላላችሁ። ይህ በተመሳሳይ ጊዜ የምትሰሩበት እና የምትማሩበት የብቃት ደረጃ ነው።

### የተማሪ ትምህርት ዕቅድ (PEP ) ስብሰባዎች

በእንክብካቤ ውስጥ ስትገቡ፣የተማሪ ትምህርት ዕቅድ (PEP ) የሚባል ፣በትምህርታችሁ ዘርፍ ላይ ድጋፍ የምታገኙባቸው ስብሰባዎች ይካሄዳሉ። የተማሪ ትምህርት ዕቅድ (PEP ) ስብሰባዎች በእያንዳንዱ የትምህርት ዓመት ሶስት ጊዜ ይካሄዳሉ። እናም ብኮሌጅ ጥሩ እንድትሰሩ ለማረጋገጥ የሚደረጉ ናቸው እንዲሁም ጥያቄዎች እንድትጠይቁ፡ ተጨማሪ ርዳታ ያስፈልጋችሁ እንደሆነም እንድታሰቡ በተጨማሪም ኮሌጅ እንዴት እየሄደ እንዳለ ሃሳባችሁን እንድታካፍሉ የሚያግዙ ናቸው።

## 2. የድህረ-16 በኋላ የትምህርት መንገዶች ምሳሌ

ከዚህ በታች ያለውን፣ እና እናንተም ልትሄዱባቸው የምትችሉ የትምህርት መንገዶች ምሳሌ ተመልከቱ፡-

| | |
|---|---|
| **ኢሶል ቅድመ- መግቢያ (ፕሪ ኢንትሪ)** | **ሂሳብ ፋንክሽናል ስኪልስ ፕሪ ኢንትሪ** |
| **ኢሶል ኢንትሪ ሌቨል 1** | **ሂሳብ ፋንክሽናል ስኪልስ ኢንትሪ ሌቨል 1** |
| **ኢሶል ኢንትሪ ሌቨል 2** | **ሂሳብ ፋንክሽናል ስኪልስ ኢንትሪ ሌቨል 2** |
| **ኢሶል ኢንትሪ ሌቨል 3** | **ሂሳብ ፋንክሽናል ስኪልስ ኢንትሪ ሌቨል 3** |
| ***ኢሶል ሌቨል 1 (በምርጫ)*** | ***ሂሳብ ፋንክሽናል ስኪልስ ሌቨል 1*** |

| | |
|---|---|
| **ሌቨል 1 የሞያ/መደበኛ ትምህርት** | **ፋንክሽናል እንግሊዝኛ እና ሂሳብ ሌቨል 1+2** |
| **ሌቨል 2 የሞያ/መደበኛ ትምህርት** | **ጂሲኤስኢ (GCSE) እንግሊዝኛ እና ሂሳብ** |


**መካከለኛ ደረጃ አፓረንትሺፕ**

**ሌቨል 3 የሞያ/መደበኛ ትምህርት**

**ዩኒቨርሲቲ**

## 3. በትምህርታችሁ ላይ የተሳተፉ፣ ቁልፍ አዋቂ ሰዎች

በትምህርታችሁ ድጋፍ በመስጠት የተሳተፉ፣ በርካታ አዋቂ ሰዎች አሉ፡-




## የማህበራዊ ጉዳዮች ባለሙያ/ የግል አማካሪ

የማህበራዊ ጉዳዮች ባለሙያ፣ ለአካባቢያችሁ መስተዳድር/ካውንስል ውስጥ የማህበራዊ አገልግሎቶች ክፍል ላይ የሚሰራ ሰው ነው። የስራ ድርሻቸው ልጆች (በዩኬ ውስጥ የሚኖሩ ከ18 ዓመት በታች የሆኑ) መጠጊያ ሲያጡ እና ወላጆቻቸው አብረዋቸው ካልኖሩ ወይ ሊንከባከቧቸው ካልቻሉ፣እንክብካቤ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ነው። የማህበራዊ ጉዳይ ባለሙያው ከኮሌጁ/ትምህርት ቤቱ ጋር በመሆን ትምህርታችሁ በጥሩ ሁኔታ እንዲቀጥል እና፣ ማናቸውንም የሚያሳስባችሁ ነገር ወይ ጉዳይ እንድታነሱ እድል እንድታገኙ የእናንተን የተማሪ ትምህርት ዕቅድ (PEP ) ስብሰባዎች በትምህርት ዓመቱ ውስጥ 3 ጊዜ ያመቻቻል። በተጨማሪም ከ18 ዓመታችሁ በኋላ የግል እስማካሪ ከማህበራዊ ጉዳዮች አገልግሎት ጋር በመስራት ይደግፉችኋል።

## የእርስዎ ተንከባካቢ

የእርስዎ ተንከባካቢ በእለት እለት ከናንተ ህይወት ውስጥ አብሮት የሚኖር ሰው ነው። ከሶሻል ሰራቶኞች ጎን በመሆን በየእለቱ ርዳታ ያደርግላችኋል ለምሳሌ፡ ከጠበቃችሁ፡ ዶክተራችሁ፡ ትምህርትቤታችሁ/ ኮሊጃችሁ ወዘተ ቀጠሮዎች ይዘዋችሁ ይሄዳሉ። ስለትምህርቱ አስቸኳይ ጥያቄ ሲኖራችሁ የእርስዎ ተንከባካቢን በመጠየቅ ድጋፍ ታገኛላችሁ ወይም ከሌሎች ባለሙያዎች መረጃዎችን ይሰበስቡላችኋል።

## የአስጠኚ/መምህር የስራ ድርሻ

አስጠኚ/መምህር፡ ኮሌጅ ውስጥ የኢሶል ትምህርቶችን የሚሰጣችሁ ሰው ነው። አስጠኚ/መምህር ኮሌጅ ውስጥ በብዛት የምታገኙት ዋናው አዋቂ ሰው ሆኖ፣ ፈተናዎቻችሁን እንድታልፉ እና በኢሶል ደረጃዎች ውስጥ እንድትሻሻሉ ያግዟችኋል።

## የምድብ መምህር የስራ ድርሻ

የምድብ መምህር የስራ ድርሻ፡ በትምህርትቤታቸው / ኮሌጃቸው ውስጥ የሚገኙ በመንግስት እንክብካቤ ስር ያሉ ልጆች (እናንተ) የትምህርት ስኬቶቻችሁን ማሳደግ ነው። የትምህርት ፍላጎቶቻችሁ እንዲሟሉ በማድረግ፣ የተቻላችሁን እንድታደርጉ እና፣ድምጾቻችሁ በትምህርት ቤቱ/ኮሌጁ ውስጥ እንዲሰማ ሃላፊነት የሚወስዱ ናቸው። የምድብ መምህር:

- **በመንግስት እንክብካቤ ውስጥ የሚገኙ ልጆች ትልልቅ ህልሞች እና ኣላማዎች እንዲኖራቸው የሚያደርጉ ባህሎችን ማስፋፋት ይገባቸዋል**
- **ኮሌጅ ውስጥ ድምጽ እንዲኖራችሁ ማድረግ አለባቸው**
- **የበለጠ ጥራት ላይ ያለው ርዳታ በመንግስት እንክብካቤ ስር ላሉ ህጻናት በትምህርትቤታቸው/ኮሌጃቸው ውስጥ እንዲያገኙ ማስቻል ይገባቸዋል**
- **በመንግስት እንክብካቤ ስር ያሉ ልጆች ፍላጎቶች ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ማስቻል አለባቸው**
- **ለትንንሽ ልጆች እና ሰራተኞች፣ የምክር እና መምሪያ ምንጮች ሆነው ማገልገል ይገባቸዋል**
- **ብኮሌጅ/ ትምህርት ቤት ውስጥ እንዴት እየሰራችሁ እንደሆነ ለመከታተል የተማሪ ትምህርት ዕቅድ (PEP ) ስብሰባዎችን ያዘጋጃሉ።**


## የባርኔት የርቀት ትምህርት ቤት ሚና

የርቀት ትምህርት ቤት ኬዝ ወርከር ድጋፍ ይኖራችኋል ከየተማሪ ትምህርት ዕቅድ (PEP ) ስብሰባዎች እና ትምህርትን በተመለከት አንተን ወክለው ከመሟገት ጎን ለጎን ይህ ኬዝ ወርከር:

- **ኮሌጃችሁ/ትምህርት ቤታችሁ የትምህርት ኣላማችሁን እንድታሳኩ እና፣ እንድትሻሻሉ እንዴት ማገዝ እንዳለባቸው እንዲረዱ ያደርጋል።**
- **አንዳንድ ጊዜ ተጨማሪ ርዳታ እንዲደረግላችሁ ያስተባብራል፣ ለምሳሌ ተጨማሪ የእንግሊዝኛ ትምህርቶች**
- **ስለትምህርታችሁ እና የመጪ ዕቅዳችሁ ምክር እና መመሪያዎችን ያቀርባል**
- **እቤት ሆናችሁ በርቀት እንድትማሩ ለመደገፍ ላፕቶፕ ያቀርባል**

## 4. በኮሌጁ የሚገኙ እድሎች

በኮሌጅ ውስጥ ልታገኟቸው የምትችሉ በርካታ እድሎች ይገኛሉ። ጥቂቶቹ እነዚህ ናቸው፡



ስፖርቶች- ኮሌጅ ውስጥ በተለምዶ ልትቀላቀሏቸው የምትችሉ የስፖርት ቡድኖች እና ልትጠቀሙባቸው የምትችሉ ጂሞች ይገኛሉ!




ቤተ-መጻሕፍት- ኮሌጅ ውስጥ ሁልጊዜ ክፍት የሆኑ ለመዝናናት የምታነቧቸውን መጽሓፍት የምትበደሩባቸው እና የምታጠኑባቸው ቤተ-መጻሕፍት ይገኛሉ።



የገንዘብ ማበረታቻ- ሁሉም ኮሌጅ ለተማሪዎች የማበረታቻ ገንዘብ (£30 የሚሆን በሳምንት) ይሰጣል። ተማሪዎች ይህንን ለመቀበል ከፍተኛ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል!

ይህ የባንክ ሂሳብ እንዲኖር ያስፈልጋል ስለዚህ መጀመርያ ላይ መቀበል ላይ ችግር ሉፈጠር ይችላል ግን በሂደት ይፈታል።




የተንከባካቢ ምክር-  ወደፊት ምን ማድረግ እንዳለባችሁ እርግጠኛ ካልሆናችሁ እያንዳንዱ ኮሌጅ እቅዳችሁን በማውጣት ላይ የሚያግዙ የስራ መመሪያ ሰራተኞች አሏቸው።

## 5. የትምህርት ዓመት የጊዜ ሰሌዳ

**በዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ የትምህርት ኣመት**

ዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ፣ ትምህርት በአጠቃላይ የሚካሄድበት የትምህርት ኣመት፣ ከመስከረም እስከ ሃምሌ የሚቆይ ነው። በዚህ ኣመት ውስጥ የዕረፍት እና የበዓል ቀናት በተለያዩ ግዜዎች ይኖሯችኋል።

### የመኽር ሴሚስተር 2021 (የኣመቱ የመጀመሪያው የትምህርት ጊዜ)

| የመኽር ሴሚስተር 2021 | ቀናት |
|---|---|
| የመጀምሪያው ሴሚስተር (የትምህርት ቤት መጀመሪያ) | እሮብ መስከረም 1- ኣርብ 22 ጥቅምት |
| ግማሽ ሴሚስተር (በዓል!) | ሰኞ ጥቅምት 25- ኣርብ ጥቅምት 29 |
| ሁለተኛ ሴሚስተር | ሰኞ 1 ህዳር - አርብ ታህሳስ 17 |
| የትምህርት በኣል | ሰኞ ታሕሳስ 20- ሰኞ ጥር 3 |

### የጸደይ ሴሚስተር 2022


| የጸደይ ሴሚስተር 2022 | ቀናት |
|---|---|
| የመጀመርያው ሴሚስተር | ማክሰኞ ጥር 4- ኣርብ ጥቅምት 11 |
| ግማሽ ሴሚስተር (በኣል) | ሰኞ ጥቅምት 14- ኣርብ ጥቅምት 18 |
| ሁለተኛ ሴሚስተር | ሰኞ ጥቅምት 21- ኣርብ ሚያዚያ 1 |
| የትምህርት በኣል | ሰኞ ሚያዚያ 4- ሰኞ ሚያዚያ 18 (የፋሲካ ሳምንት ሚያዚያ 15-18) |

### የበጋ ሴሚስተር 2022 (የኣመቱ የመጨረሻው የትምህርት ጊዜ!)

| የበጋ ሴሚስተር 2022 | ቀናት |
|---|---|
| የመጀመርያው ሴሚስተር | ማክሰኞ ሚያዚያ 19- ኣርብ ግንቦት 27 (ግንቦት 2 ላይ የመይደይ ባንክ ሆሊደይ) |
| ግማሽ ሴሚስተር (በኣል) | ሰኞ ግንቦት 30- ኣርብ ሰኔ 3 (የጸደይ ባንክ ሆሊደይ ሰኔ 2 ላይ ከተጨማሪ ባንክ ሆሊደይ ሰኔ 3 ጋር ይካሄዳል) |
| ሁለተኛ ሴሚስተር | ሰኞ ሰኔ 6- ኣርብ ሃምሌ 22 |
| የትምህርት በኣል | ሰኞ ሃምሌ 25 - ሃሙስ መስከረም 1 |

## 6. የምሳሌ ኮሌጅ የጊዜ ሰሌዳ

ከዚህ በታች ያለው የትምህርት ቀናቶቻችሁ እንዴት እንደሚወሰኑ የሚያሳይ የምሳሌ ኮሌጅ የጊዜ ሰሌዳ ነው። አብዛኞቹ ኮሌጆች በሳምት 4 ቀናት እንድትማሩ ይጠይቃሉ



## 7. ጠቃሚ ሊንኮች

### ጠቃሚ አድራሻዎች

ባርኔት የርቀት ትምህርት ቤት
Barnet.virtualschool@barnet.gov.uk
0208 359 4534

ኒው ሲቲዝንስ ጌትዌይ (ባርኔት የስደተኞች አገልግሎት)
ኒው ሲቲዝንስ ጌትዌይ (ባርኔት የስደተኞች አገልግሎት) (ncgateway.org.uk)
info@ncgateway.org.uk
07983 437 425

የስደተኞች ካውንስል (ረፊዩጂ ካውንስል)
https://www.refugeecouncil.org.uk
info@refugeecounci.org.uk
02073466700

### ለትምህርት ጠቃሚ ሊንኮች እና መረጃ

https://elt.oup.com/student/headway/?cc=gb&selLanguage=en
ሄድ ዌይስ የእንግሊዘኛ ኦንላይን- ከጀማሪ እስከ የላቀ ደረጃ ጽሑፎች ሰዋሰው፡ መዝገበ ቃላት፡ የእለት እለት እንግሊዘኛ እና ፈተናዎች

https://www.britishcouncil.org/school-resources/find
ደረጃዎችን በመፈለግ ላይ የሚያግዝ የኦንላይን ትምህርት ከነጻ የእንግሊዘኛ ፈተናዎች ጋር። የመስማት እና የማንበብ መጻሕፍት እና የሰዋሰው እና የመዝገበ ቃላት ክፍሎች። በተለይ እንግሊዘኛ እንደተጨማሪ ቋንቋ ለሚጠቀሙ እና UMC ዩኤምቢሲ ጥሩ ነው።

https://www.perfect-english-grammar.com
ፍጹም የእንግሊዘኛ ሰዋሰው ሁሉንም ጉዳዮች የሸፈኑ የእንግሊዘኛ ሰዋሰው ትምህርቶች ።

https://www.gamestolearnenglish.com
ይህ ተማሪዎች እንግሊዘኛ መማር የሚችሉበት የነጻ ድረ-ገጽ ነው። ተማሪዎች እንግሊዘኛን አዝናኝ በሆነ መንገድ መማር የሚችሉባቸው የተመረጡ ጨዋታዎች ይገኛሉ።

የነጻ የእንግሊዘና ትምህርቶች ለስደተኞች| ኮንቨርሳሽን አቨር ቦርደርስ
ኮንቨርሳሽን ኦቨር ቦርደርስ የጥገኝነት ጥያቄ ያቀረቡ እና ስደተኞችን ፣ከበጎ ፈቃድ ኣስጠኚዎች ጋር እንዲገናኙ እና፣ በነጻ አንድ ለ አንድ ኦንላይን ላይ የሚደረገውን የንግግር ትምህርቶች እንዲያገኙ  ያደርጋል። ይህ እንግሊዘኛ በመናገር ረገድ የራስ መተማመንን ለማጎልበት የሚያግዝ፣ በሰብአዊ መገናኛዎች አማካኝነት ድንበሮች እንዲገናኙ ያደርጋል።

የመኖሪያ ፈቃድ- የጥገኝነት ጉዞዎች  (youngasylumguide.org.uk)
ለጥገኝነት ጉዞዎች የሚጠቅሙ አስፈላጊ መመሪያዎች